# የቴሌኮምኒኬሽን ኔትዎርክ ኢንተርኮኔክሽን መመሪያ ማብራሪያ ሰነድ

## 1. መግቢያ

ኢትዮጵያ የቴሌኮም ኢንዱስትሪ ገበያን ለሃገር ውስጥ እና ለውጪ ሃገር ባለሃብቶች ክፍት እንዳደረገች ይታወቃል። በዚህም ምክንያት በመንግስት እጅ የቆየው ሴክተር ላይ ከአንድ በላይ የሆኑ የቴሌኮም ኦፐሬተሮች እንዲሁም ሌሎች አገልግሎት ሰጪዎች ይሳተፋሉ ተብሎ ይጠበቃል። በዚህም ምክንያት በአገልግሎት ሰጪዎች መካከል የሚፈጠሩ የቴሌኮምኒኬሽን ኔትዎርከ ኢንተርኮኔክሽንን የተመለከቱ ጉዳዮች ጎልተው ይወጣሉ። በኮምኒኬሽን አገልግሎት አዋጅ ቁጥር 1148/2012 አንቀ 6(13) እና 43 (1) ላይ በኦፐሬተር/አገልግሎት ሰጪ አካላት መካካል የሚፈጠር የኢንተርኮኔክሽን ሁኔታ ምን መልክ ሊኖረው እንደሚገባ ጠቅለል ባለ መልኩ ተቀምጧል።

እነዚህን አጠቃላይ ድንጋጌዎች ወደ መሬት ለማውረድ እና በኦፐሬተሮች/አገልግሎት ሰጪዎች መካከል ተገቢ የሆነ የኢንተርኮኔክሽን ስርሃት እንዲዘረጋ በዘርፉ ዝርዝር ድንጋጌዎችን ማወጣት ያስፈልጋል። ይህን መሰርት በማድረግ የቴሌኮምኒኬሽን ኔትዎርክ ኢንተርኮኔክሽን መመሪያ የተዘጋጀ ሲሆን ይህም በዘርፉ ውጤታማ ስራን መስራት ያስችላል ተብሎ ይታመናል።

## 2. የመመሪያው የሕግ መሰረት

የኢትዮጵያ ኮሙኒኬሽን ባለሥልጣን በኮሙኒኬሽን አገልግሎት አዋጅ ቁጥር 1148/2011 አንቀጽ 6(13) ላይ በተለያዩ የቴሌኮምኒኬሽን አገልግሎት ሰጪዎች መካከል የሚኖረውን የቴሌኮምኒኬሽን ኔትዎርኮች ኢንተርኮኔክሽን አንደሚቆጣጠር ተገልጿል። ከዚህ በተጨማሪም የአዋጁ አንቀጽ 43(1) ባለስልጣኑ የኢንተርኮኔክሽን ስምምነትን በተመለከተ መመሪያ እንደሚያወጣ የሚያመለክት ሲሆን የአዋጁ አንቀጽ 54 (2)ም ይህኑ ያረጋግጣል።

## 3. የመመሪያው ዓላማ

ይህ መመሪያ የተለያዩ አላማዎችን ከግብ ለማድረስ የተዘጋጅ ሲሆን በዚህ ክፍል ዋና ዋና ሊባሉ የሚችሉ የመመሪያውን አላማዎች ተመልከተዋል፤-

- የቴሌኮም አገልግሎት ሰጪዎች የተናበበ እና የተሰላሰለ የቴሌኮምኒኬሽን አገልግሎት በመላው ሃገሪቱ ውስጥ እንዲሰጡ ማስቻል፤

- በቴሌኮም አገልግሎት ሰጪዎች መካከል የሚደረግ የቴሌኮም ኔትዎረክ ኢንተርኮኔክሽን ስምምነት የሚመራበት እና የሚተዳደርበት አጠቃላይ የህግ ፍሬምዎርክ ማበጀት፤
- በቴሌኮም አገልግሎት ሰጪዎች መካከል የሚደረግ የቴሌኮም ኔትዎርክ ኢንተርኮኔክሽን ስምምነቶች ላይ ግልጽነትን መፍጠር እና የተፋጠነ ስምምነት ላይ እንዲደርሱ ማስቻል፤
- የአንድ የቴሌኮምኒኬሽን አገልግሎት ሰጪ ተጠቃሚዎች በሃገሪቱ ውስጥ ከሚሰራ ሌላ የቴሌኮምኒኬሽን አገልግሎት ተጠቃሚዎች ጋር መገናኘት የሚችሉበትን እድል መፍጠር፤

**4. የመመሪያው የዝግጅት ሂደት**

የመመሪያው ዝግጅት ከአንድ አመት በላይ የወሰደ እና በርካታ ሂደቶችም ያለፈ ሲሆን ረቂቅ ህጉ ተጠናቅቆ እስከቀረበበት ድረስ የተከናወኑ አበይት ተግባራት ወይም ሂደቶች በሚከተለው መልኩ ተጠቃልሏል።

- **ጥናት ማካሄድ፦** እስካሁን ድረስ የቴሌኮም ዘርፉ ለገበያ ክፍት ባለመሆኑ ከዘርፉ ጋር ተያይዞ የሚነሱ የህግ ጥያቄዎችን በበቂ ሁኔታ የሚያስተዳደር የቴሌኮምኒኬሽን ኔትዎረክ ኢንተርኮኔክሽን ስምምነትን የተመለከተ ህግ እና የአሰራር ልምድ አልነበረንም። በመሆኑም ዘርፉን መሰረት ያደረገ ህግ ለመቅረጽ ጥናቶች ማካሄድና በጥልቀት መረዳት የሚጠይቅ ነው። ይህንን ለማሳካት የሃገሪቱ ነባራዊ ሁኔታ፣ በዘርፉ የዳበረ ልምድ ያላቸው የሃገራት ተሞክሮ እና የቴክኖሎጂ እድገት በተመለከተ ጥናት ተደርጎል። በዚህ ጥናት አማካኝነት በረቂቅ መመሪያ ውስጥ ሊካተቱት የሚገባቸው ድንጋጌዎች እና ዋና ዋና ቁም ነገሮች ጉዳዮች ተለይቷል።
- **ለረቂቅ ህጉ ዝግጅት ግብአት የሚሆኑ ሞዴል ህጎችና ተሞክሮዎች መምረጥ፦** የቴሌኮም ዘርፍ ላይ አለም-አቀፍ ተቋማት ተሳታፊ በመሆናቸው ዘርፉን የሚያስተዳድረው ህግም አለምአቀፍ ደረጃውን በጠበቀ መልኩ መዘጋጀት አለበት። ስለሆነም የህጉ ይዘት አለም አቀፍ ደረጃው የጠበቀ ይሆን ዘንድ ከሃገሪቱ ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ እና ፖለቲካዊ ሁኔታዎች አንጻር ተቀራራቢ የሆኑ ሃገራት ህጎች በሞዴልነት ተመርጠዋል፦
- **ባለድርሻ አካላትን ማወያየት፦** ረቂቅ መመሪያውን ለማዳበር የሚከተሉት ሶስት የውይይት መድረኮች ተዘጋጅተዋል፦
    - የሃገር ውስጥ እንዲሁም አለማቀፍ የቴሌኮም ኦፕሬተሮችን፣ ከዘርፉ ጋር ግንኙነት ያላቸው የመንግስት እና የግል ባለደርሻ አካላትን፣ የሲቪክ ማህበረሰብን፣ ዘርፉ ላይ የሚሰሩ የህግ

ባለሙያዎችን ፣ባለሃብቶችን ወዘተ ተሳታፊ ያደረገ የአንድ ወር[1] የምክክር መድረክ ተዘጋጅቷል።

- ረቂቁን በባለስልጣኑ ዌብሳይት ላይ ለ20 ቀናት ለሕዝብ አሰተያየት ክፍት እንዲሆን ተደርጎ፤ ፍላጎቱ ካላቸው የሃገር ውስጥ እንዲሁም አለማቀፍ ተቋማት በቂ የሆነ ግባት ለመሰብሰብ ተችሏል።
- የተሰበሰቡ ግባቶች በመመሪያው ላይ ስለተካተቱበት ሁኔታና ተያያዥ ጉዳዮች ሰስተኛ የምክክር መድረክ ተዘጋጅቷል።

## 5. በረቂቅ መመሪያው ላይ የተነሱ ነጥቦች እና የተወሰዱ እርምጃዎች

በረቂቅ መመሪያው ላይ የተለያዩ የሃገር ውስጥ እና የውጪ ሃገር ባለድርሻ አካላት ተሳታፊ የሆኑ ሲሆን በመድረኩ ላይ የተለያዩ ጥያቄዎች ተነስተዋል። ከነዚህም ውስጥ የሚከተሉት ዋና ዋና ናቸው።

- በመግቢያ (preamble) ክፍል ላይ መመሪያውን ማውጣት ያስፈለገበት ዋና ዋና ምክንያቶች ተለይተው በአንድ ወይም ሁለት ፓራግራፍ ውስጥ እንዲካተት ቢደረግ፤
- መመሪያውን ማሻሻል በተመለከተ ክፍል ላይ መመሪያው በማንኛውም ወቅት እንደሚሻሻል ተደንግጓል። ይህ ግን የባለፍቃዶችን ጥቅም ስለሚጎዳ መመሪያው ሲሻሻል ባለድርሻ አካላት ተሳታፊ የሚሆኑበት ሁኔታ ቢፈጠር።
- በመመሪያው ላይ የተመለከቱ እና ትርጓሜ የሚያሰፈልጋቸው ቃላቶች ትርጓሜ ቢሰጣቸው።
- የኢንተርኮኔክሽን ስምምነቶች በሀገሪቱ የህግ አስፈጻሚና የደህንነት ተቋም ላይ ተጸዕኖ እንደማይኖረው ቢረጋገጥ፤
- የባለስልጣኑ ስልጣን የኢንተርኮኔክሽን ግጭቶች የሚፈቱበት ሁኔታን ማመቻቸት ሳይሆን መፍታት ነው።በመሆኑም በመመሪያው አንቀጽ 5(1)(ሀ) ላይ የተመለከተው ድንጋጌ ቢሻሻል።
- ባለስልጣኑ የኢንተርኮኔክሽን ክፍያ ሲወሰን በምን መልክ መወሰን አለብት የሚለው ላይ በግልጽ ቢመለከት። በ long incremental cost (LRIC) መሰረት ቢሰራ ገበያውን ለውደድር ዝግጁ እና ምቹ ያደርገዋል።
- ኢትዮ ቴሌኮም ኢንተርኮኔክሽን በተመለከተ ጉልህ የገበያ ድርሻ እንዳለው ቢወሰን፤

[1] https://eca.et/2019/10/10/initial-stakeholder-consultation/

- የዚህን መመሪያ ድንጋጌ በአግባቡ በማይተገብሩ አካላት ላይ የሚጣለውን ቅጣት ወይም አስተዳደራዊ እርምጃ በመመሪያው የልዩ ልዩ ድንጋጌዎች ክፍል ውስጥ ቢመላከት። በአዋጁ አንቀፅ 52 (4-6) በተመላከተው መሰረት የህግ ማስፈፅሚያ ዝርዝሮች በሚኒስትሮች ምክር ቤት ወጥተው ከሆነ በልዩ ልዩ ክፍል ቢካተቱ ያልወጡ ከሆነ ደግሞ ደንቡ በቶሎ እንዲወጣ ቢደረግ ይህ ካልሆነ ካለ ደንቡ መመሪያውን ማስፈፀም አዳጋች ያደርገዋል።
- በመመሪያው ላይ ትርጉም የሚያስፈልጋቸው ነገር ግን ትርጉም ያልተሰጣቸው ቃላቶች ትርጉም ቢሰጣቸው።

ከላይ የተመለከቱት እና ሌሎች ተያያዥ ጥያቄዎች ላይ ሰፊ ውይይት የተደረገ ሲሆን ባለስልጣኑም የሃገሪቱን ጥቅም እና የዘርፉ መስፋፋት የሚኖረውን ፋይዳ ግንዛቤ ውስጥ በመክትት የሚከተሉት ውሳኔዎች ተወስነዋል፡-

- ኢትዮቴሌኮም በዘርፉ ጉልህ የገበያ ድርሻ አለው ተብሎ መመሪያው ላይ ይመልከት ተብሎ የተነሳው ጥያቄ ተገቢ አይደለም። አንድ ኦፕሬተር በአንድ ዘርፍ ላይ ጉልህ ድርሻ አለው የሚባለው በአዋጁ እና አዋጁን ተከትለው የወጡ መስፈርቶችን መሰረት በማድረግ ነው። ከዚህ በተጨማሪም አንድ ኦፕሬተር ጉልህ የገበያ ድርሻ አለው ተብሎ በመመሪያ መወሰን አዳጋች ነው። ምክንያቱ ደግሞ ዛሬ ላይ ጉልህ የገበያ ድርሻ አለው ተብሎ የተሰየመው ኦፕሬተር ነገ ላይ ጉልህ ድርሻ ላይኖረው ስለሚችል።
- የቴሌኮም ኔትዎረክ ኢንተርኮኔክሽን ስምምነት ደህንነትን ከግንዛቤ የከተተ መሆን አለበት የሚለው ጥያቄ ተገቢነት ያለው ሲሆን ይህ ግን ሃገሪቱ ባወጣቻቸው ሌሎች ህጎች በቂ ምላሽ ያገኝ በመሆኑ እዚህ ቦታ ላይ መድገሙ አስፈላጊ አይደለም።
- በመመሪያው መግቢያ ላይ የተነሳው ጥያቄ አግባብነት ያለው በመሆኑ ማሻሻያ ተደርጓበታል።
- መመሪያውን ባለስልጣኑ በማንኛውም ወቅት እንደሚያሻሽለው የተመለከተው ንግግር የአገልግሎት ሰጪዎችን ፍላጎት ስለሚጎዳ ይሻሻል የሚለው ጥያቄ ተገቢነት ስላለው ማሻሻያ ተደርጎበታል።
- በመመሪያው ውስጥ ለተካተቱ እና ፍቺ ለሚያስፈልጋቸው ቃላቶች ፍቺ ተሰጥቷቸዋል።

- የባለስልጣኑ ስልጣን የቴሌኮም ኔትዎርክ ኢንተርኮኔክሽን የተመለከቱ ግጭቶች የሚፈቱበት ሁኔታን ማመቻቸት ሳይሆን መፍታት ነው የሚለው አስተያየት ተገቢነት ስላለው በማሻሻያ ውስጥ እንዲካተት ተደርጓል።
- ባለስልጣኑ የቴሌኮም ኔትዎርክ ኢንተርኮኔክሽን ክፍያ ሲወሰን በምን መልክ መወሰን አለብት የሚለው ነጥብ በግልጽ ይቀመጥ የሚለው አስተያየት ተቀባይነት ስላለው በመመሪያው ላይ ማሻሻያ ተደርጓበታል፤
- ከቅጣት ጋር ተያይዞ የቀረበው ሐሳብ ተገቢ አስተያየት እንደሆነ በመቀበል ማሻሻያው ግን በዚህ ህግ ሳይሆን ወደ ፊት በሚወጣው ደንብ መሰረት የሚመለስ እንደሆነ ግንዛቤ ተወስዶበታል።

### 6. ለውይይት የተሰራጨው ረቂቅ መመሪያ እና የመጨረሻ ሆኖ የወጣው መመሪያ

- በማስታወቂያ በተሰራጨው መመሪያ ላይ ባለስልጣኑ መመሪያውን በማንኛውም ወቅት እንደሚያሻሽለው ተመልክቷ የነበረ ሲሆን በመጨረሻ ረቂቅ ላይ ግን ባለስልጣኑ መመሪያውን ሲያሻሽል ከባለድርሻ አካላት ጋር በጉዳዩ ዙሪያ ውይይት ማድረግ እንደሚኖርበት ተመልክቷል። ይህ የተደረገበት ዋና ምክንያት ባለስልጣኑ በየወቅቱ ባለድርሻ አካላትን ሳያሳትፍ ማሻሻያ የሚያደርግ ከሆነ የአገልግሎት ሰጪዎችን ፍላጎት/ጥቅም ይጎዳል ከሚል ሐሳቤ የተነሳ ሲሆን ይህም ከባለድርሻ አካላትም በኩል በስፋት ሲንጸባረቅ ነበር። ጥያቄው የአዋጁን መንፈስ ያገናዘበ እና ተገቢ በመሆኑ እንዲስተካከል ተደርጓል።
- በመመሪያው መግቢያ ላይ ለመመሪያው መሰረት የተደረጉ ድንጋጌዎች ብቻ ናቸው የተካተቱት። ለመመሪያው መውጣት ምክንያት የሆኑ ነጥቦች አልተካተቱም የሚል አስተያት ከባለደርሻ አካላት በኩል ቀርቧል። ስለሆነም የመመሪያው መግቢያ የመመሪያውን አስፈላጊነት አጉልቶ በሚያሳይ መልኩ በድጋሚ ይስተካካል የሚለው ሐሳቤ/ አስተያት ተገቢ በመሆኑ በዛ መልክ እንዲስተካከል ተደርጓል።
- በመድረክ ተሳታፊዎች ፍቺ የሚያስፈልጋቸው ቃላቶች ተለይተው የቀረቡ ሲሆን ለእነዚህ ቃላቶች ትርጓሜ ተሰጥቷቸዋል።
- ለምክክር በቀረበው ሰነድ ላይ ባለሰልጣኑ የቴሌኢንተርኮኔክሽን ስምምነትን የተመለከቱ ግጭቶችን እንዲፈቱ ሁኔታዎችን ያስተባብራል ተብሎ ተገለጸው አስተያየት ለባለሰልጣኑ በአዋጅ

ከተሰጠው ስልጣን ጋር የሚቃረን በመሆኑ ኢንትርኮኔክሽን በተመለከተ የሚነሱ ልዩነቶች ወይም ግጭቶችን ይፈታል በሚል እንዲተካ ተደርጓል።

- ባለስልጣኑ የቴሌኮም ኔትዎርክ ኢንተርኮኔክሽን ክፍያ ሲወሰን በምን መልክ መወሰን አለብት የሚለው ነጥብ በግልጽ ለውይይት የቀረበው ሰነድ ላይ አልተመለከተም የሚለው ጥያቄ ተቀባይነት ስላገኘ መመሪያው ላይ ማሻሻያ ተደርጓበታል። በዚህም መሰረት የቴሌኮም ኔትዎርክ የኢንተርኮኔክሽን ክፍያ በምን መልክ እና ምን ምን ሁኔታዎችን ከግምት ከቶ እንደሚወስን በግልጽ በማሻሻያው ላይ ተመልክቷል።